ረቂቅ

# የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር

# የተሻሻለ መመስረቻ ፅሁፍ

**ታህሳስ 2015 ዓ.ም**

**ረቂቅ**

# ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር

## የተሻሻለ መመስረቻ ፅሁፍ

## መግቢያ

ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር (ከዚህ በኋላ "ባንኩ" እየተባለ ይጠቀሳል) በ1952 ዓ.ም. በወጣው የንግድ ህግ እና የባንክ ሥራን ስለመፍቀድና ስለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/1986 መሰረት በተዘጋጀው የመመስረቻ ፅሁፍና መተዳደሪያ ደንብ ተቋቁሞ በመስራት ላይ ያለ በመሆኑ፣

የ1952ቱ ንግድ ህግ በአዲሱ የንግድ ህግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 (ከዚህ በኋላ "ንግድ ህጉ" እየተባለ ይጠቀሳል) በመሻሻሉና እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 84/1986 በአዋጅ ቁጥር 592/2000 (በአዋጅ ቁጥር 1159/2011 እንደተሻሻለው) በመተካቱ፣

አዲሱ የንግድ ህግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀፅ 177 እና 255 የአክሲዮን ማህበር ለማቋቋምም ሆነ ለመምራት አስፈላጊው ሰነድ የመመስረቻ ፅሁፍ ብቻ መሆኑን በመደንገጉ፣

ስለሆነም አሁን በስራ ላይ ያሉትን የባንኩን መመስረቻ ፅሁፍና መተዳደሪያ ደንብ በማዋሃድ የተዘጋጀውን ይህንን የተሻሻለ መመስረቻ ፅሁፍ የባንኩ ባለአክሲዮኖች 19ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ እንደሚከተለው አፅድቋል፡፡

### አንቀፅ 1

### የባንኩ መጠሪያ ስም

ባንኩ "ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር" ተብሎ ይጠራል፡፡

### አንቀፅ 2

### ዋና መ/ቤት

1. የባንኩ ዋና መ/ቤት በአዲስ አበባ ነው፡፡
2. ባንኩ በኢትዮጵያ በማናቸውም ስፍራ ወይም ከኢትዮጵያ ውጭ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ቅርንጫፍ እና/ወይም ተጠሪ ፅ/ቤት ማቋቋም ይችላል፡፡

### አንቀፅ 3

### የባንኩ ዓላማ እና ተግባር

ባንኩ የሚከተሉት ዓላማዎችና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

## ረቂቅ

1. የቁጠባ፣ የተንቀሳቃሽና በጊዜ ገደብ የተወሰነ ተቀማጭ ገንዘብ መቀበል፤
2. ብድር፣ አድቫንስና የኦቨር ድራፍት አገልግሎት መስጠት፤
3. በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ ተከፋይ የሚሆኑ የሐዋላ ወረቀቶችን፤ የክፍያ ትዕዛዞችንና የተስፋ ሰነዶችን ማውጣት፣ መቀበል፣ በቅናሽ መግዛት፣ መሸጥና መለወጥ፤
4. በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ ተቀባይነት ያላቸው ቼኮችንና የመንገደኛ ቼኮችን ማውጣት፣ መቀበልና መሸጥ፤
5. የንግድ ዋስትናዎችን መስጠት፤
6. ዓለም አቀፍ የባንክ ስራዎችን መስራትና በባንኮች መካከል በሚካሄዱ የንግድ ስራዎች መሰማራት፤
7. የካዝና አገልግሎት መስጠት፣
8. የመንግስትና የግል ዋስትና ሰነዶችን ገዝቶ በመሸጥ ስራ ኢንቨስት ማድረግና በአክሲዮን ልውውጥ/ በስቶክ ኤክስቼንጅ/ ስራ መሳተፍ፤
9. አክሲዮን ለሚገዙና ለሚሸጡ ወኪል ሆኖ መስራት፤
10. እንደ አስፈላጊነቱ ሀብት/ገንዘብ ኢንቨስት ማድረግ፤
11. ለንግድ ባንኮች የተፈቀዱ ማናቸውንም አይነት ሌሎች ስራዎች መስራት።

### አንቀፅ 4

### የባንኩ ካፒታል

1. የባንኩ የተፈረመ ካፒታል ብር 10,000,000,000.00(አስር ቢሊየን) ነው።
2. የባንኩ የተከፈለ ካፒታል ብር 5,000,000,000.00(አምስት ቢሊየን) ነው።
3. ካፒታሉ እያንዳንዳቸው ብር 500(አምስት መቶ) ዋጋ ባላቸው 20,000,000(ሀያ ሚሊየን) ተራና የተመዘገቡ አክሲዮኖች ተከፋፍሏል።
4. እያንዳንዱ ባለአክሲዮን በግሉ ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር በጋራ ሊኖረው የሚችለው ከፍተኛ አክሲዮን በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ከተገለፀው የባንኩ ካፒታል ከመቶ ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል በባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀፅ 11 መሰረት የሚወሰን ሆናል።
5. ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ማህበሮች የባንኩን አክሲዮን መግዛት ይችላሉ።
6. እያንዳንዱ ባለአክሲዮን የፈረመውና የከፈለው አክሲዮን ብዛት በፅሁፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ተደርጎ ይቀመጣል።

### አንቀፅ 5

### የካፒታል ማሳደግ

1. አዳዲስ አክሲዮኖች በማውጣት ወይም ያሉትን አክሲዮኖች ዋጋ ከፍ በማድረግ የባንኩን ካፒታል ማሳደግ ይቻላል። ሆኖም የአዲስ አክሲዮን ዋጋ የክፍያ ጊዜ ከአምስት ዓመት አይበልጥም።
2. የሚወጡት አዳዲስ አክሲዮኖች ለነባር አባላት ወይም ለአዳዲስ አባላት እንዲሸጡ ሊወሰን ይችላል።

ረቂቅ

3. የአዳዲስ አክሲዮኖች አወጣጥ፣ አመዳደብና አሻሻጥ በንግድ ህጉ አንቀፅ 445 እና ተከታዮች ድንጋጌ መሰረት ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 6

## አክሲዮኖች

1. የባንኩ አክሲዮኖች በሙሉ በባለአክሲዮኑ ስም የተመዘገቡ፣ የማይከፋፈሉና እኩል ዋጋ ያላቸው ተራ የወረቀት አክሲዮኖች ናቸው፡፡
2. እያንዳንዱ አክሲዮን አንድ ድምፅ ይኖረዋል፡፡
3. ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች የባንኩ አክሲዮን የጋራ ባለሃብት ከሆኑ የንግድ ህጉ አንቀፅ 270(2፣3 እና 4) ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
4. አንድ ባለአክሲዮን ሲሞት አክሲዮኖቹ ለህጋዊ ወራሾች ይተላለፋሉ፡፡
5. በአክሲዮኖች ላይ ቀሪ ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነትን በሚመለከት የንግድ ህጉ አንቀፅ 289 ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
6. ዝቅተኛው የባንኩ አዲስ ባለአክሲዮን የመሆን መጠን 200(ሁለት መቶ) አክሲዮን ነው፡፡ ሆኖም ይህ ዝቅተኛው አክሲዮን መጠን በህግ በተረጋገጠ የወራሽነት ማረጋገጫ ወይም በፍ/ቤት ትዕዛዝ የሚተላለፍን አክሲዮን አይመለከትም፡፡

## አንቀፅ 7

## የባለአክሲዮኖች መዝገብ

1. በንግድ ህጉ አንቀፅ 274 መሰረት አስፈላጊ የሆነውን መረጃ የያዘ የባለአክሲዮኖች መዝገብ በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት ይቀመጣል፡፡ መዝገቡ በወረቀት ወይም ለረጅም ዘመን በሚቆይ የኤለክትሮኒክ ዘዴ መያዝ ይችላል፡፡
2. የባለአክሲዮኖች መዝገብን በተመለከተ የንግድ ህጉ አንቀፅ 274 ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት አላቸው፡፡

## አንቀፅ 8

## የአክሲዮን ሰርተፊኬት

1. የአክሲዮን ሰርተፊኬት የሚሰጠው በሙሉ ለተከፈለባቸው የተመዘገቡ አክሲዮኖች ሲሆን ሰርተፊኬቱ በንግድ ህጉ አንቀፅ 273 ላይ የተገለፁትን ነገሮች ይይዛል፣ ቁጥርም ይሰጠዋል፡፡
2. እያንዳንዱ የአክሲዮን ሰርተፊኬት ታትሞ፣ በአንድ ዳይሬክተርና በባንኩ ፕሬዚዳንት/ ዋና ስራ አስፈፃሚ ተፈርሞና የባንኩ ማህተም ተደርጎበት ባለአክሲዮኑን በማስፈረም ይሰጣል፡፡
3. አንድ የአክሲዮን ሰርተፊኬት ቢበላሽ፣ ቢሰረቅ፣ ቢወድቅ ወይም ቢጠፋ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚወስነውን ክፍያ በማስከፈል እና ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ የጠፋውን ሰርተፍኬት

በማንኛውም መንገድ የያዘ አካል ካለ በ15 ቀን ውስጥ ለባንኩ እንዲያሳውቅ በማድረግ ሰርተፍኬቱን ይዤዋለሁ የሚል ካልቀረበ ማደስ ወይም መተካት ይቻላል።

4. የባንኩ ባለአክሲዮን መሆን የሚቻለው በባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 (በአዋጅ ቁጥር 1159/2011 እንደተሻሻለ) አንቀፅ 2(9) መሰረት ዜግነትን በተመለከተ የተቀመጠውን ገደብ መሰረት በማድረግ ነው።

## አንቀፅ 9

## አክሲዮን ስለማስተላለፍ

1. አክሲዮኖች በባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 (በአዋጅ ቁጥር 1159/2011 እንደተሻሻለ) አንቀፅ 2(9) መሰረት ዜግነትን በተመለከተ የተቀመጠውን ገደብ መሰረት በማድረግ ሊተላለፉ ይችላሉ።
2. የአክሲዮኖች መተላለፍ በባለአክሲዮኖች መዝገበ ካልተመዘገበ ውጤት አይኖረውም።
3. የባንኩን ጥቅም ሊጎዳ ይችላል ተብሎ በቦርዱ የታመነበት ሰው በቦርዱ ውሳኔ ባለአክሲዮን እንዳይሆን ገደብ ሊደረግበት ይችላል።

## አንቀፅ 10

## የባለአክሲዮኖች መብት

1. በንግድ ህጉ፣ በባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 (በአዋጅ ቁጥር 1159/2011 እንደተሻሻለ)፣ አግባብነት ባለው የብሄራዊ ባንክ መመሪያ እንዲሁም ሌሎች በየጊዜው በሚወጡ የባለአክሲዮኖች መብቶችን በሚመለከቱ የህግ ድንጋጌዎች ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን የሚከተሉት መብቶች አሉት።
   - 1.1. በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔዎች ላይ የመሳተፍና ድምፅ የመስጠት፣
   - 1.2. በከፈለባቸው አክሲዮኖች መጠን ከባንኩ ዓመታዊ የተጣራ ትርፍ ላይ የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ የማግኘትና ባንኩ ሲፈርስ ከዕዳ የሚተርፈውን ቀሪ ገንዘብ የመካፈል፤
   - 1.3. የባንኩ ካፒታል ከፍ ሲል አዲስ የሚወጡ አክሲዮኖችን በያዛቸው አክሲዮኖች ድርሻ መጠን ለመግዛት ቅድሚያ የማግኘት፣
   - 1.4. በዚህ መመስረቻ ፅሁፍ አንቀፅ 9(1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ አክሲዮኖችን የመሸጥ፣
   - 1.5. መያዣው በአክሲዮን መዝገብ እንዲመዘገብ በማድረግ አክሲዮኖቹን በመያዣነት የመስጠት መብት አለው።
2. አንድ አክሲዮን በመያዣነት ወይም በአላባ መብት በሚያዝበት ጊዜ የንግድ ህጉ አንቀፅ 271 ተፈፃሚ ይሆናል።

ረቂቅ

3. የአንድ ባለአክሲዮን ጥቅም ከባንኩ ጥቅም ጋር የሚጋጭ ከሆነ ባለአክሲዮኑ በድምፅ መስጠት መብቱ አይጠቀምም።

**አንቀፅ 11**

**ኃላፊነት**

1. የባንኩ ኃላፊነት ባለው ሀብት መጠን የተወሰነ ይሆናል።
2. የባለአክሲዮኖች ኃላፊነት የፈረሙትን አክሲዮን ዋጋ በመክፈል ላይ የተወሰነ ነው። ሆኖም ወሳኝ ድምጽ ያላቸውን ባለአክሲዮኖች በተመለከተ በንግድ ህጉ አንቀፅ 295 የተመለከተው ተፈፃሚ ይሆናል።

**አንቀፅ 12**

**የባንኩ ስራ አመራር አካላት**

1. የባንኩ የአመራር አካላት፡-
   - 1.1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ፣
   - 1.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ፣
   - 1.3. ኦዲተሮች፣
   - 1.4. ፕሬዚዳንት/ዋና ስራ አስፈፃሚ እና ሌሎች የማኔጅመት አባላት፣
   - 1.5. የባንኩ ፀሐፊ

   ናቸው።

**አንቀፅ 13**

**የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ**

1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ መደበኛ፣ አስቸኳይ ወይም ልዩ ሊሆን ይችላል።
2. የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ እንደነገሩ ሁኔታ በዳይሬክተሮች ቦርድ፣ በኦዲተሮች፣ በብሄራዊ ባንክ፣ በፍ/ቤት፣ በሂሳብ አጣሪዎች ወይም ጠቅላላ ጉባዔው በንግድ ህጉ አንቀፅ 331 መሰረት ወደፊት የተቆጣጣሪ ቦርድ እንዲኖረው ከወሰነ በተቆጣጣሪ ቦርዱ ሊደረግ ይችላል። እንዲሁም ከባንኩ ዋና ገንዘብ ቢያንስ አምስት በመቶ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ እንዲጠራ ለፍ/ቤት ማመልከት ይችላሉ።
3. አንድ ባለአክሲዮን በአግባቡ ሥልጣን በሰጠው ወኪሉ አማካኝነት በጠቅላላ ጉባዔ ድምፅ መስጠት ይችላል። ተወካዩ ባለአክሲዮን ላይሆንም ይችላል። በውክልና ድምፅ መስጠትን በተመለከተ አግባብነት ያለው የብሄራዊ ባንክ መመሪያ ተፈፃሚ ይሆናል።
4. የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ የሚደረገው ጉባዔው ከሚደረግበት 24(ሀያ አራት) ቀናት በፊት ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ፣ በብሮድካስት ሚዲያ ወይም አመቺ በሆነ ኤሌክትሮኒክ ሚዲያ ይሆናል።

**ረቂቅ**

5. በባለአክሲዮኖች ወይም በወኪሎቻቸው የሚፈረም በእያንዳንዱ ጉባዔ የተገኙ አባላት ዝርዝር በየጠቅላላ ጉባዔው ተዘጋጅቶ ይቀመጣል። ዝርዝሩም በቦርድ ሊቀመንበር፣ በፀሐፊውና በድምፅ ተቀባዮች ፊርማ ይረጋገጣል።
6. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ የጉባዔው ሰብሳቢ ይሆናል፤ ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢው፣ ምክትል ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ከዳይሬክተሮች መካከል በሹመት ቀደምትነት ያለው፣ ቀደምትነት ያለው በማይኖርበት ጊዜ ደግሞ ጠቅላላ ጉባኤው የሚመርጠው ሰው ሰብሳቢ ይሆናል።
7. አምስት ከፍተኛ ባለአክሲዮኖች ከመካከላቸው የሚመርጧቸው ሁለት ባለ አክሲዮኖች የጠቅላላ ጉባዔ ድምፅ ተቀባዮች ወይም ቆጣሪዎች ሆነው ይመደባሉ፤ የባንኩ ፀሀፊ የጠቅላላ ጉበዔዎች ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል።
8. በጠቅላላ ጉባዔዎች ላይ የተደረጉ ውይይቶች በንግድ ህጉ አንቀፅ 387(3) መሰረት በሚዘጋጅ ቃለ-ጉባዔ ይያዛሉ። በንግድ ህጉ አንቀፅ 387(1) መሰረት የጠቅላላ ጉባዔ ቃለ-ጉባዔዎች በስብሰባው በተገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና የባንኩ ፀሀፊ ይፈረማሉ።
9. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች በንግድ ህጉ አንቀፅ 391(1) መሰረት በሁሉም ባለአክሲዮኖች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## <u>አንቀፅ 14</u>

## <u>መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ</u>

የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የንግድ ህጉ አንቀፅ 393(2) በሚፈቅደው መሰረት ከባንኩ የሂሳብ ዓመት መጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ይካሄዳል።

### 1. <u>ምልዓተ-ጉባዔ</u>

1.1. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ መጀመሪያ ሲጠራ ድምፅ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ቢያንስ የባንኩ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) አንድ አራተኛውን የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ እንደተሟላ ይወሰዳል።

1.2. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው ለሁለተኛ ጊዜ ሲጠራ ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖች የሚወክሉት ዋና ገንዘብ ግምት ውስጥ ሳይገባ በተገኙት ባለአክሲዮኖች ውሳኔዎችን ማሳለፍ ይችላል።

1.3. ጉባዔው ውሳኔ የሚሰጠው ተራ በሆነ የድምፅ ብልጫ ነው። ለድምፅ አቆጣጠር ድምፅ ተዐቅቦና ያልተፃፈባቸው የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ካሉ ከግምት ውስጥ አይገቡም።

### 2. <u>ስልጣንና ተግባር</u>

ሌሎች በህግ ለጉባዔው የተሰጡ ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ጉባዔው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

2.1. የሂሳብ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ፣ እንዲሁም የቦርድንና የኦዲተሮችን ሪፖርቶች መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት፣

2.2. በትርፍ ድርሻ ክፍፍል እንዲሁም ካለፈው የሂሳብ ዓመት ጋር ተያይዘው በሚነሱ የሂሳብ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ መስጠት፣

2.3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን፣ የውጭ ኦዲተሮችን፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴዎችን መምረጥ፣ ማሰናበትና አበላቸውን መወሰን፣

2.4. የዳይሬክተሮችን ቁጥር መጨመር ወይም መቀነስ እንዲሁም ዳይሬክተሮች የቦርዱን ሥራ የሚለቁበትን ሁኔታ መወሰን፣

2.5. ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ከተሰጡት በስተቀር በሌሎች ጉዳዮች ላይ ሁሉ ውሳኔ መስጠት፣

**<u>አንቀፅ 15</u>**

**<u>አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ</u>**

አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን በማናቸውም ጊዜ ሊጠራ ይችላል፡፡

**1. <u>ምልዓተ-ጉባዔ</u>**

ምልዓተ ጉባዔው ተሟልቷል የሚባለው በሚከተሉት ሁኔታዎች ነው፡-

1.1. በመጀመሪያው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ውስጥ ቢያንስ የባንኩን ዋና ገንዘብ አንድ ሶስተኛ የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው የተገኙ እንደሆነ፤

1.2. በሁለተኛው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ውስጥ ቢያንስ የባንኩ ዋና ገንዘብ አንድ አራተኛ የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው የተገኙ እንደሆነ፤

1.3. በሶስተኛው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖች የሚወክሉት ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ግምት ውስጥ ሳይገባ በስብሰባው በተገኙት አባላት፡፡

**2. <u>ስልጣንና ተግባር</u>**

2.1. ሌሎች በህግ ለጉባዔው የተሰጡት ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ጉባዔው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

2.1.1. የባንኩን መመሥረቻ ፅሁፍ ማሻሻል፣

2.1.2. ባለአክሲዮኖች የካፒታል ኢንቨስትመንታቸውን በፈቃደኝነት እንዲጨምሩ ማድረግ፣

2.1.3. የባንኩን ዋና ገንዘብ የማሳደግ ወይም የመቀነስ፤ ሆኖም ካፒታሉ የሚያድገው የነባር አክሲዮኖችን ዋጋ (par value) ከፍ በማድረግ ከሆነ የባለአክሲዮኖችን ሙሉ ድጋፍ ይፈልጋል፣ ይህ ቢኖርም የአንዱ አክሲዮን ዋጋ ከፍ እንዲል የተደረገው ከባንኩ መጠባበቂያ ገንዘብ ወይም ሊከፋፈል ከሚችል ትርፍ በመውሰድ ከሆነ ግን የባለአክሲዮኖችን ሙሉ ድጋፍ አያስፈልግም፡፡

**ረቂቅ**

2.1.4. ድምፅ የመስጠት መብት ባላቸው ባለአክሲዮኖች ሙሉ ድጋፍ የባንኩን ዜግነት መለወጥ፣

2.1.5. ባንኩ እንዲፈርስ፤ ወደ ሌላ ዓይነት የንግድ ማኅበር እንዲለወጥ፣ እንዲከፋፈል ወይም እንዲዋሀድ የመወሰን፡፡

2.2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2.1(2.1.1) ላይ የተመለከተው ቢኖርም የባንኩን ባለአክሲዮኖች ስም፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣ የያዙት የአክሲዮን ብዛትና የተከፈለውን የገንዘብ መጠን በተመለከተ የሚደረጉ ለውጦች የባንኩን መመስረቻ ፅሁፍ እንደማሻሻል አይቆጠሩም፡፡

2.3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2.1(2.1.3 እና 2.1.4) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ የፀና የሚሆነው በጉባዔው የተገኙት ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖች ከወከሉት ካፒታል ሁለት ሦስተኛውን በሚወክሉት ድምጽ ከተደገፈ ነው፡፡ ለድምጽ ብልጫው አቆጣጠር ስሌት ድምጽ ያልሰጡም ሆነ ድምጽ ያልተጻፈባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ግምት ውስጥ አይገቡም፡፡

2.4. አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው አስፈላጊው ምልዓተ-ጉባኤ ባለመሟላቱ ምክንያት ሳይሰበሰብ የቀረ እንደሆነ ሁለተኛ ስብሰባ፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ሦስተኛ ስብሰባ በአንድ ሳምንት ልዩነት ውስጥ በንግድ ህጉ አንቀፅ 366 እና 367 መሰረት መጠራት አለበት፡፡

## <u>**አንቀፅ 16**</u>

## <u>**የዳይሬክተሮች ቦርድ መሰየም፣ ስልጣንና ተግባር**</u>

1. ባንኩ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጡ 12 (አስራ ሁለት) ዳይሬክተሮች በሚገኙበት ቦርድ ይመራል፡፡ የቦርድ አባላቱ አግባብነት ባለው የብሔራዊ ባንክ መመሪያ ላይ የተቀመጠውን ስብጥርና አስፈላጊውን መስፈርት ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፡፡
2. አግባብነት ባላቸው የንግድ ህጉ ድንጋጌዎች፣ የባንክ ስራ አዋጆች እና የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ለዳይሬክተሮች ቦርድ የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

2.1. የባንኩን ስራዎች በበላይነት መምራትና መቆጣጠር፣

2.2. ባንኩ ጤናማ የፋይናንስ አስተዳደር፣ በቂ ዋና ገንዘብ እና ክፍያዎችን በወቅቱ የመፈፀም አቅም ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፣

2.3. የባንኩን የአደጋ ተጋላጭነት እና ውስጣዊ አሰራር ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣

2.4. ባንኩ ብሄራዊ ባንክ ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች የሚያሟላ የብድር ግምገማ ስርዓት መዘርጋቱን ማረጋገጥ፣

2.5. የጠቅላላ ጉባዔ እና የቦርድ ስብሰባዎችን ቃለ-ጉባዔ፣ የሂሳብ መዝገብ፣ የአክሲዮን መዝገብ፣ በንግድ ህጉ አንቀፅ 311 መሰረት ከባንኩ ጋር ቅርበት ያላቸው ሰዎች የተባሉትን መዝገብ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች እንዲያዙ ማድረግ፣

2.6. ለጠቅላላ ጉባዔው ጥሪ ከሚደረግበት ቢያንስ ከ55 (አምሳ አምስት) ቀናት በፊት የማኀበሩ የንብረት ዝርዝር፣ የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ፤ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ እና የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ለኦዲተሮች እና ለብሄራዊ ባንክ መላክ፣

2.7. የባንኩን ባለአክሲዮኖች ጉባዔ መጥራት፤ የፋይናንስ እንቅስቃሴን ያካተተ ዓመታዊ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ለጉባዔው ማቅረብ፣

2.8. የባንኩ ካፒታል ሶስት አራተኛ ሲጠፋ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ መጥራት፤

2.9. አግባብነት ባለው ህግ፣ በዚህ መመስረቻ ፅሁፍ እና በጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ መሰረት መቋቋም ያለባቸውን መጠባበቂያ ሂሳቦች ማቋቋምና መያዝ፤

2.10. የዳይሬክተሮች ቦርድ እጩ ጥቆማና ምርጫ አፈፃፀም መመሪያ አዘጋጅቶ እንዲፀድቅ ወይም እንዲሻሻል ለመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ማቅረብ፣

2.11. የባንኩ የውጭ ኦዲተሮች ሹመት እና የስራ ዋጋ እንዲፀድቅ ለመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ማቅረብ፣

2.12. የባንኩን ፕሬዚዳንት/ዋና ስራ አስፈፃሚ መሾም፣ መሻር፣ ደመወዝና አበሉን መወሰን፣

2.13. የባንኩ ፕሬዚዳንት/ዋና ስራ አስፈፃሚ በሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ መሰረት የባንኩን ምክትል ፕሬዚዳንቶች/ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚዎችን፣ የውስጥ ኦዲት መምሪያ ዳይሬክተርን፣ የሪስክና ኮምፕሊያንስ መምሪያ ዳይሬክተርን እና የባንኩ ፀሀፊ ሹመት፣ ምደባና ስንብት ላይ መወሰን፣

2.14. የባንኩን መዋቅራዊ አደረጃጀት እና የሰራተኞች ደመወዝ፣ ስኬልና ጥቅማ ጥቅም ማፅደቅ፣

2.15. በጠቅላላ ጉባዔ ከሚወሰኑት በስተቀር የባንኩን ፖሊሲዎች ማፅደቅ፤ ማሻሻል፣

2.16. የባንኩን ስትራቴጂክ ዕቅድ፤ ዓመታዊ እቅድና በጀት ማፅደቅ፤ አፈፃፀማቸውን መከታተል፣

2.17. የባንኩ ካፒታል እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ለጠቅላላ ጉባዔው ሀሳብ ማቅረብ፤

2.18. ወሳኝ በሆኑ የባንኩ ኢንቨስትመንት፣ ቋሚ ንብረት እና ቴክኖሎጂ ግዢና ሽያጭ በሚመለከት ውሳኔ መስጠት፣

2.19. የግዴታ ወረቀቶችን ማውጣት፣ ከዚያምጋር የተያያዙትን ዋስትናዎች ማፅደቅ፣

**ረቂቅ**

2.20. ለባንኩ ስራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከውጭ ሀገር ባንኮችና የፋይናንስ ተቋማት ገንዘብ ለመበደር የሚቀርብ የውሳኔ ሀሳብን ማፅደቅ፣

2.21. ገንቢ መስሎ የሚታየውን ማንኛውንም ሀሳብ ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ማቅረብ፣

2.22. ለጠቅላላ ጉባዔ ባልተሰጡ ሌሎች ስልጣኖች መስራት፣

2.23. አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ የዳይሬክተሮች ቦርድ የተወሰኑ ስልጣኖቹን በዝርዝርና ግልፅ በሆነ መልኩ ለማናቸውም የቦርድ አባል ወይም ለባንኩ የስራ መሪዎች በውክልና ወይም በቃለ-ጉባዔ መስጠት።

## <u>አንቀፅ 17</u>

## <u>የዳይሬክተሮች ምርጫና የዋስትና አክሲዮን</u>

1. ዳይሬክተሮች ለሦስት ዓመት ጊዜ ለማገልገል ይመረጣሉ።
2. ዳይሬክተሮች በጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ መሠረት በሥራ ዘመናቸው መጨረሻ እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ ሊመረጡ ይችላሉ።
3. የቦርዱን ሥራ ቀጣይነት ለማረጋገጥ ጠቅላላ ጉባዔው የተወሰኑትን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ለሶስተኛ ጊዜ ሊመርጥ ይችላል። ሆኖም ለሶስተኛ ጊዜ የሚመረጡት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቁጥር ከጠቅላላ የቦርድ አባላቱ አንድ ሦስተኛ (1/3) አይበልጥም።
4. ዳይሬክተሮች ከመካከላቸው አንድ ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር ይመርጣሉ።
5. የቦርድ ሊቀመንበር የቦርዱን ስብሰባዎች ይመራል፣ እሱ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሊቀመንበሩ ስብሰባውን ይመራል፣ ሁለቱም በማይኖሩበት ጊዜ በስብሰባው የሚመረጠው ዳይሬክተር ስብሰባውን ይመራል።
6. በንግድ ህጉ አንቀፅ 302 መሰረት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ለተጣለባቸው ኃላፊነት የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና ያስይዛሉ። ዋስትናው የቦርድ አባላቱ የከፈሉባቸውን የባንኩ የአክሲዮን ሰርተፍኬቶችን ለባንኩ በመስጠት ማስያዝ የሚችሉ ሲሆን መጠኑም በአክሲዮን ሰርተፍኬቶቹ ላይ በተፃፈው የዋጋ መጠን መሰረት ተሰልቶ ቢያንስ እስከ ብር 100,0000(አንድ መቶ ሺህ ብር) መሆን አለበት። በቦርድ አባልነት የተመረጠው ባለአክሲዮን በቂ አክሲዮን ከሌለው ቀሪውን በሚመለከት ሌላ ዋስትና ሊያቀርብ ይችላል።
7. የቦርድ አባሉ በንግድ ህጉ 296(2) መሰረት ባለአክሲዮን ባይሆንም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ተደርጎ የተመረጠ ከሆነ ለዋስትናው ተመጣጣኝ የሆነ ከላይ መጠኑ የተገለፀውን ገንዘብ ብር 100,0000(አንድ መቶ ሺህ ብር) ለባንኩ ማስያዝ አለበት።
8. ዋስትናው ቀሪ የሚሆነው የቦርድ አባላቱ ስራቸውን ሲለቁ እና በሥራ ላይ በነበሩበት ጊዜ ከባንኩ የሚፈለግባቸው ዕዳ የሌለ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው።

ረቂቅ

## አንቀፅ 18
## ውድድርን ስለመከልከልና በባንኩና በዳይሬክተሮች መካከል ስለሚደረጉ ግንኙነቶች

1. ጠቅላላ ጉባዔው ካልፈቀደ በቀር ዳይሬክተሮች በተወዳዳሪ ማህበሮች ማህበርተኛ አይሆኑም። እንዲሁም በራሳቸውም ስም ሆነ በሦስተኛ ወገኖች ስም የባንኩ ተወዳዳሪ አይሆኑም።
2. በባንኩና በማንኛውም ዳይሬክተር መካከል ወይም በባንኩና ማንኛውም ዳይሬክተር ባለቤት፣ አባል፣ ወኪል፣ ዳይሬክተር ወይም ሥራ አስኪያጅ በሆነበት ድርጅት መካከል የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት በቅድሚያ በቦርዱ መፅደቅና ኦዲተሮቹም እንዲያውቁት መደረግ አለበት።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) ከተገለፀው በተጨማሪ የንግድ ህጉ አንቀፅ 320 እና አግባብነት ያለው የብሄራዊ ባንክ መመሪያ ተፈፃሚ ይሆናሉ።
4. በንግድ ህጉ አንቀፅ 311 መሰረት ከባንኩ ጋር ቅርበት ያላቸው ሰዎች የተባሉትን መዝገብ በባንኩ ዋና መ/ቤት የሚቀመጥ ሲሆን ዝርዝሩና በመዝገቡ ላይ ለውጦች ሲደረጉ ለሚመለከታቸው አከላት ማሳወቅና አስፈላጊ ተግባራት ሁሉ ይፈፀማሉ።

## አንቀፅ 19
## የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ በባንኩ ዋና መ/ቤት ወይም በማንኛውም ሌላ ቦታ ሊደረግ ይችላል።
2. ምልዓተ ጉባዔው የሚኖረው ቁጥራቸው ከግማሽ በላይ የሆኑ ዳይሬክተሮች ሲገኙ ነው። እያንዳንዱ ዳይሬክተር አንድ ድምፅ ብቻ ይኖረዋል።
3. አንድ ዳይሬክተር የእሱን ሥራና ኃላፊነት በሚመለከት ጉዳይ ድምፅ አይሰጥም።
4. የቦርድ ስብሰባዎች የሚጠሩት በሊቀመንበሩ ወይም እሱ በማይኖርበት ጊዜ በምክትል ሊቀመንበሩ ይሆናል። ጥሪ የሚደረገውም የስብሰባውን አጀንዳ በማያያዝ ለዳይሬክተሮች በሙሉ በሚደርስ ማስታወቂያ ይሆናል።
5. የቦርድ ሊቀመንበር ወይም እሱ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሊቀመንበር የቦርዱን ስብሰባዎች ይመራል። ሁለቱም በማይኖሩበት ጊዜ የስብሰባው ሊቀመንበር በተገኙት ዳይሬክተሮች ይመረጣል።
6. የዳይሬክተሮች ቦርድ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል ሊቀመንበሩ እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።
7. ከስብሰባ የቀረ አንድ ዳይሬክተር የሚወከለው ስብሰባው ላይ በሚገኝ ሌላ ዳይሬክተር ብቻ ይሆናል። የውክልና ሥልጣኑ በፅሁፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ይሰጣል። አንድ ዳይሬክተር ሊወከል የሚችለው ለአንድ ዳይሬክተር ብቻ ነው።
8. ውሳኔዎች የሚያልፉት በድምፅ ብልጫ ይሆናል። ድምፅ እኩል ለእኩል በሚሆንበት ጊዜ ሊቀመንበሩ የሚደግፈው ድምፅ የቦርዱ ውሳኔ ይሆናል።

**ረቂቅ**

9. የቦርዱ ውሳኔዎች በቃለ ጉባዔ ተፅፈው በስብሰባው ላይ በተገኙት ዳይሬክተሮች ይፈረማሉ። ቃለ ጉባዔውም ለዚሁ በተዘጋጀ መዝገብ ውስጥ ይቀመጣል።
10. ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ስርዓት ደንብ ያወጣል።
11. የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባውን በንግድ ህጉ አንቀፅ 308 እና 309 እንዲሁም አግባብነት ባለው የብሄራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ያደርጋል። ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ስብሰባውን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ሊያደርግ ይችላል።

**አንቀፅ 20**

**የዳይሬክተሮች አበልና የሥራ ዋጋ**

ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሚከፈለው ዓመታዊ የስራ ዋጋ እና ወርሀዊ አበል መጠን አግባብነት ባለው የብሄራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት በጠቅላላ ጉባዔው ይወሰናል።

**አንቀፅ 21**

**የዳይሬክተሮች መለወጥና መነሳት**

1. አንድ ዳይሬክተር፡-
   1.1. ለቦርዱ በፅሁፍ በማስታወቅ የዳይሬክተርነቱን ሥራ ሲለቅ ወይም
   1.2. የቦርዱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ባለማክበር ወይም በሌላ ምክንያት ሲነሳ የቦርድ አባሉ በሌላ ዳይሬክተር ይተካል። ይህንኑ የተተካ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ቦርዱ ለቀጣዩ ጠቅላላ ጉባዔ አቅርቦ ያፀድቃል።
2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል መተካትን በሚመለከት የንግድ ህጉ አንቀፅ 303፣ የብሄራዊ ባንክ መመሪያ እንዲሁም የባንኩ ጠቅላላ ጉባዔ ያፀደቃቸው መመሪያዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

**አንቀፅ 22**

**ኦዲተሮች**

**1. ሹመትና የስራ ዘመን**

1.1. ጠቅላላ ጉባዔው የባንኩ የውጭ ኦዲተሮችን እና ተለዋጭ ኦዲተሮችን ይሾማል፣ የስራ ዋጋቸውንም ይወስናል።

1.2. የውጭ ኦዲተሮች እና ተለዋጭ ኦዲተሮች ለሦስት ዓመታት እንዲያገለግሉ በጠቅላላ ጉባዔ ይሾማሉ።

**2. ስልጣንና ተግባር**

2.1. በንግድ ህጉ አንቀፅ 348፣ በባንክ ስራ አዋጆች እና በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ለኦዲተሮች የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ኦዲተሮች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል።

2.1.1. የባንኩን መዛግብትና የገንዘብ ዋስትና ሠነዶችን መመርመር፣

ረቂቅ

2.1.2. የባንኩ ንብረት በትክክል ተመዝግቦ መያዙን፣ መተዳደሩንና መጠበቁን እንዲሁም የሂሳብ ሚዛኖች የትርፍና የኪሳራ መግለጫዎች በትክክል መሠራታቸውን ማረጋገጥ፣

2.1.3. ስለባንኩ ሁኔታ ቦርዱ ያቀረበው ሪፖርት ትክክል መሆኑ ማረጋገጥ፣

2.1.4. ለዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ሪፖርት ማቅረብ፣

2.1.5. ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን ለቦርዱ ወይም ለጠቅላላ ጉባዔው እንዲሁም ወንጀል መፈፀሙን ሲረዱ ለዐቃቤ ሕግ ማስታወቅ፣

2.1.6. በሕጉ ወይም በመመሥረቻ ፅሁፉ መሠረት ቦርዱ ጠቅላላ ጉባዔውን ካልጠራ መጥራት፣

2.1.7. የባንኩን የፋይናንስና የሥራ አመራር በሚመለከት በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ምርመራ ማካሄድ፣

2.1.8. በጠቅላላ ጉባዔ የሚሰጣቸውን ልዩ ተግባራት መፈፀም።

## <u>አንቀፅ 23</u>

## <u>የባንኩ ፕሬዚዳንት/ዋና ስራ አስፈፃሚ</u>

1. ፕሬዚዳንቱ/ዋና ስራ አስፈፃሚው የሚሾመው፣ ደመወዝና የአገልግሎት ጊዜውም የሚወሰነው በዳይሬክተሮች ቦርድ ይሆናል።
2. የፕሬዚዳንቱ/ዋና ስራ አስፈፃሚው ተግባርና ስልጣን በዚህ የተሻሻለ መመስረቻ ፅሁፍ እና አግባብነት ባለው የብሄራዊ ባንክ መመሪያ ላይ እንደተወሰነው ይሆናል።

## <u>አንቀፅ 24</u>

## <u>የፕሬዚዳንት/ዋና ስራ አስፈፃሚ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ፕሬዚዳንቱ የባንኩ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሲሆን ከዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ፣ በዚህ መመሥረቻ ፅሁፍና አግባብ ባላቸው ህጎች መሠረት የባንኩን ሥራ ያካሄዳል።
2. ከዚህ በላይ የተጠቀሰው አተቃላይ አገላለፅ እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሬዚዳንቱ/ዋና ስራ አስፈፃሚው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

   2.1. የባንኩን አላማዎች ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ስራዎችን ሁሉ በባንኩ ስም መስራት፤ የባንኩን የየዕለት የስራ እንቅስቃሴ መምራት፣

   2.2. የባንኩን ምክትል ፕሬዚዳንቶች/ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚዎችን፣ የውስጥ ኦዲት መምሪያ ዳይሬክተርን፣ የሪስክና ኮምፕሊያንስ መምሪያ ዳይሬክተርን እና የባንኩ ፀሀፊ ሹመት፣ ምደባና ስንብት ለቦርዱ አቅርቦ ማስወሰን፣

   2.3. የባንኩን ድርጅታዊ መዋቅር ማዘጋጀት፣ በቦርዱ ሲፀድቅ ስራ ላይ ማዋል፣

   2.4. በፀደቀው ድርጅታዊ መዋቅር መሰረት አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞችን መቅጠር፣ ማስተዳደር እና በህግ አግባብ ማሰናበት፣

   2.5. የባንኩን እስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎች አዘጋጅቶ እንዲፀድቅ ለቦርዱ ማቅረብ፣

2.6. የባንኩን የስራ መመሪያዎችና የቁጥጥር ስርዓት ማውጣት፣ ማፅደቅ፣ በስራ ላይ ማዋል፣

2.7. ለባንኩ ስራ አስፈላጊና አስተማማኝ የሆነ የኢንፎርሜሽን ሲስተም በማዘጋጀት እንዲፀድቅ ለቦርዱ ማቅረብ፤ ሲፀድቅም በስራ ላይ ማዋል፣

2.8. ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ማንኛውንም አይነት ግንኙነት ባንኩን መወከል፣

2.9. በብሄራዊ ባንክ መመሪያዎች መሰረት ገንዘብ ማበደር፣ አድቫንስና የኦቨር ድራፍት ብድር መስጠት፣ በዓለም አቀፍ የባንክ ስራ ላይ ባንኩ እንዲሳተፍ ማድረግ፣

2.10. በባንኩ ስም በሌላ ባንክ ወይም ባንኮች የባንክ ሂሳብ መክፈትና ማንቀሳቀስ፣ በባንኩ ስም አስቀድሞ የተከፈቱትን የባንክ ሂሳቦችንም ማንቀሳቀስ፣

2.11. ቼክ፣ የሚተላለፉ ሰነዶች፣ እንደ የሃዋላ ወረቀት ያሉ የንግድ ሠነዶችን ማውጣት፣ መፈረም፣ መቀበልና ማስተላለፍ፣

2.12. ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ፣ ከሀገር ውስጥ ባንኮችና የፋይናንስ ተቋማት ገንዘብ መበደር፣

2.13. ከላይ ለቦርዱ በአንቀፅ 16(2.18) የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ባንኩ ከፎርክሎዠር ጋር በተያያዘ የተረከባቸውን ንብረቶች፣ ጉዳት የደረሰባቸው ወይም በእርጅና ምክንያት መወገድ የሚገባቸው ተሸከርካሪዎችና ሌሎች ንብረቶች እንዲሁም ከባንኩ መደበኛ ስራ ጋር በተገናኘ ሌሎች የባንኩ የሚንቀሳቀሱ እና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች እንዲሸጡ/እንዲወገዱ መወሰን፣

2.14. ባንኩ የሚያከናውናቸውን የቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት ግዥና ሽያጭ ውል፣የኪራይ ውል መፈራረም፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይህንኑ ስልጣኑን ለባንኩ ሰራተኞች በውክልና መስጠት፣

2.15. የባንኩን ሂሳብ አያያዝ መምራትና መቆጣጠር፣

2.16. የሂሳብ ዓመቱ ከመጀመሩ ቢያንስ ከሁለት ወር በፊት የባንኩን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ማዘጋጀትና ቦርዱ እንዲያፀድቀው ማቅረብ፣

2.17. የሥራ ክንውን ሪፖርት በየሦስት ወሩና የሂሳብ ሪፖርት በየዓመቱ ለቦርዱ ማቅረብ፣

2.18. ቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የባንኩን የህብረት ስምምነት ተደራድሮ መፈረም፣

2.19. የባንኩን ቅርንጫፍ መክፈትና መዝጋት፣

2.20. ከዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ማከናወን፣

2.21. እንደአስፈላጊነቱ ድምፅ የመስጠት ሥልጣን ሳይኖረው በቦርዱ ስብሰባ መሳተፍ፣

2.22. ከተሰጡት ሀላፊነቶች መካከል ለሌሎች የባንኩ የማኔጅመንት አባላትና ሰራተኞች በውክልና ማስተላለፍ።

**<u>አንቀፅ 25</u>**

**ረቂቅ**

**<u>የባንኩ ፀሐፊ</u>**

1. የባንኩ ፀሀፊ ቅጥርና ስንብት በፕሬዚዳንቱ/ዋና ስራ አስፈፃሚው አቅራቢነት በቦርዱ የሚጸድቅ ይሆናል::
2. የባንኩ ጠቅላላ ጉባዔዎችን እና የዳይሬክተሮች ቦርድ ፀሐፊ በመሆን ቃለ-ጉባዔዎችን ይይዛል፡፡
3. የባንኩ ፀሀፊ ተጠሪነት ለፕሪዚዳንቱ ሲሆን በንግድ ህጉ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

**<u>አንቀፅ 26</u>**

**<u>የትርፍ ክፍፍል</u>**

1. በባንኩ ሂሳብ ዓመት መጨረሻ የትርፍ ክፍፍል የሚደረገው ጠቅላላና አስተዳደራዊ ወጪዎች፣ ሌሎች ወጪዎች፣ ህጋዊ መጠባበቂያ ሂሳብና ሌሎች መጠባበቂያ ሂሳቦች በህጉና በዚህ የተሻሻለ መመስረቻ ፅሁፍ መሰረት ከተቀነሱ በኋላ ነው፡፡
2. ከላይ የተጠቀሰው ትርፍ ለባለአክሲዮኖች የሚከፋፈለው በከፈሉት የአክሲዮን ይዞታ መጠን ይሆናል፡፡
3. የትርፍ ክፍፍል መቼና እንዴት መፈፀም እንዳለበት በዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ይወሰናል፡፡
4. የባንኩ ዋና ገንዘብ ላይ ጉድለት ከደረሰ ይህ ጉድለት ስለመወገዱ ብሄራዊ ባንክ በባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀፅ 18(4) መሰረት እስኪያረጋግጥ ድረስ ባንኩ ለባለአክሲዮኖች የትርፍ ክፍፍል አይፈፅምም፡፡

**<u>አንቀፅ 27</u>**

**<u>የትርፍ ድርሻና መጠባበቂያ ሂሳብ</u>**

1. የትርፍ ድርሻ ሊከፈል የሚችለው በጠቅላላ ጉባዔው በፀደቀው የሂሳብ ሚዛን ላይ ከሚታየው የተጣራ ትርፍ ላይ ብቻ ነው፡፡
2. የንግድ ሕጉ እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የትርፍ ድርሻ እንዲከፈል ሐሳብ ከማቅረቡ በፊት ከባንኩ ትርፍ ላይ ተገቢ ሆኖ ያገኘውን ያህል የተወሰነ ገንዘብ በመቀነስ የባንኩን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በሚጠቅም ሥራ ላይ የሚውል መጠባበቂያ ሂሳብ መያዝ ይችላል፡፡ እንዲሁም ቦርዱ የተባለውን ገንዘብ ለመጠባበቂያ ሂሳብ መመደቡን በመተው አግባብ ሆኖ ካገኘው ማናቸውም ትርፍ ሳይከፋፈል ወደሚቀጥለው ዓመት እንዲተላለፍ ለባንኩ ጠቅላላ ጉባዔ ሃሳብ ማቅረብ ይችላል፡፡
3. ባንኩ በማናቸውም የትርፍ ድርሻ ላይ ወለድ እንዲከፍል አይጠየቅም፡፡

**<u>አንቀፅ 28</u>**

**<u>የባንኩ ሂሳብ</u>**

**ረቂቅ**

1. ባንኩ በንግድ ሕግ በተደነገገው መሠረት የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፣ በየሂሳብ ዓመቱ መጨረሻም የሂሳብ ሚዛንና የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ያዘጋጃል፡፡
2. ባንኩ ህጋዊ መጠባበቂያ ሂሳቡ ካፒታሉን እስኪያህል ድረስ በየዓመቱ ከተጣራ ትርፍ ላይ 25% እያነሳ ወደዚሁ መጠባበቂያ ሂሳብ ያስተላልፋል፡፡
3. ጠቅላላ ጉባዔው ሌሎች መጠባበቂያ ሂሳቦች ማቋቋም ይችላል፡፡
4. የሂሳብ ሚዛን የትርፍና ኪሳራ መግለጫ የዳይሬክተሮች ቦርድና የኦዲተሮች ሪፖርቶች ለዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ይቀርባሉ፡፡

## አንቀፅ 29
## ስለመፍረስና ሂሳብ ማጣራት

ባንኩ የሚፈርሰውና ሂሳብ የሚጣራው በንግድ ህጉ አንቀፅ 589(2) እና በባንክ ስራ አዋጆች ላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 30
## የሂሳብ ዓመት

የባንኩ የሂሳብ ዓመት በየዓመቱ እ.ኤ.አ ጁላይ 01 ቀን እስከ ጁን 30 ቀን ድረስ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 31
## ሪፖርቶች

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ለእያንዳንዱ የሂሳብ ዓመት የሂሳብ ሚዛንና የትርፍና ኪሳራ መግለጫ እንዲሁም የስራ ክንውን ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከቱት የሂሳብ መግለጫዎችና ሪፖርት በቦርዱ ከተዘጋጁ በኋላ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ከመጠራቱ ከ55 (አምሳ አምስት) ቀናት በፊት ለውጭ ኦዲተሮች ይቀርባሉ፡፡

## አንቀፅ 32
## ህትመት

1. ባንኩ የሂሳብ መግለጫዎቹን አግባብነት ባለው ህግ መሰረት ታትመው እንዲወጡ ያደርጋል፡፡
2. ባንኩ የራሱ የሆነ ድረ-ገፅ ይኖረዋል፡፡ በድረ-ገፁ ላይ በንግድ ህጉ አንቀፅ 493 እና 494 የተመለከቱት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀፅ 33
## የባንኩ ማህተም

ቦርዱ የባንኩ ማህተም በጥንቃቄ እንዲያዝ ያደርጋል፣ ማህተሙም የሚደረግበት ማናቸውም ሠነድ ሥልጣን በተሰጠው የባንኩ የሥራ መሪ ይፈረማል፡፡

## አንቀፅ 34

**ረቂቅ**

## ባንኩ የሚቆይበት ጊዜ

ባንኩ ላልተወሰነ ጊዜ እንዲቆይ የተመሰረተ ነው።

## አንቀፅ 35

## የባንኩ መመስረቻ ፅሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ስለመሻሻላቸውና ስለመጠቃለላቸው

1. የባንኩ የቀድሞ መመስረቻ ፅሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ተጠቃለው በዚህ የተሻሻለ መመስረቻ ፅሁፍ ተተክተዋል።
2. ሆኖም የባንኩ መስራች ባለአክሲዮኖችን በተመለከተ በቀድሞው መመስረቻ ፅሁፍ መግቢያ፣መጨረሻና በአንቀፅ 1 ላይ የተጠቀሰው ባለበት ሁኔታ ይቀጥላል።

## አንቀፅ 36

## መመሥረቻ ፅሁፉን ስለማሻሻል

1. ይህ የተሻሻለ መመሥረቻ ፅሁፍ በንግድ ህጉ አንቀፅ 400(1) መሰረት በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ማሻሻል ይቻላል።
2. የመመሥረቻ ፅሁፍን ማሻሻል በተመለከተ አግባብነት ያላቸው የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## አንቀፅ 37

## ተፈፃሚ ህጎች

በዚህ የተሻሻለ መመስረቻ ፅሁፍ ባልተጠቀሱ ጉዳዮች ላይ የንግድ ህጉ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የኢትዮጵያ ህጎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## አንቀፅ 38

## መመስረቻ ፅሁፉ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ የተሻሻለ መመስረቻ ፅሁፍ ዛሬ ታህሳስ 06 ቀን 2015 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ በተደረገው የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር ባለአክሲዮኖች 19ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የፀደቀ ሲሆን በብሄራዊ ባንክ ታይቶ ሲፈቀድና በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

# ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር